## መመሪያ ቁጥር 811/2013

**ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤና ጎጂ የሆኑ ወይም የመውለድ ሁኔታ የሚያውኩ ስራዎችን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ**

### መግቢያ

ሴት ሠራተኞች በሥራ ላይ ሲሰማሩ ከተለያዩ የስራ ላይ አደጋዎች እና የጤና ጉዳቶች ለመከላከል በተለይም ከባድ ወይም ለጤና ጎጂ ከሆኑ ወይም የመውለድ ሁኔታን ከሚያውኩ ሥራዎች ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይኸ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### 1. አውጪው ባለስልጣን

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 171/1/መ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው ጉጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ሥራዎችን እንደገና ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 811/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ማለት ነው፡፡

## Directive No. 811/2021

**Directive on types of works which are particularly hazardous or dangerous to the health and to the reproductive systems of women workers**

### Introduction

This Directive has been issued in order to protectwomen workers from occupational injuries or damages to their health that may result from engaging in work that is heavy, harmful to health, or that adversely affects child childbirth.

### 1. Legislating Authority

The Ministry of Labor and Social Affairs has issued this Directive in accordance with the authority vested on it by Labor Proclamation No. 1156/2011 Article 171/1/d.

### 2. Short Title

This Directive may be cited as "**Directive on types of works which are particularly hazardous or dangerous to the health and to the reproductive systems of women workers**" **Directive No 811/2021.**

### 3. Definitions

For the implementation of this Directive:

1. "Proclamation" means Labour proclamation No. 1156/2019.

2. **"ከባድ ሥራ"** ማለት በደቂቃ ከ7.0 ኪሎ ካሎሪ በላይ የሆነ ሜታቦሊክ ኢነርጂ ወይም ጉልበት የሚጠይቅ የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

3. **"ተከታታይነት ያለው ሥራ"** ማለት የሥራው እንቅስቃሴ የመቋረጥ ባሕሪይ የሌለበት እና የድግግሞሽ ሂደት የሚታይበት ሆኖ አካላዊ ጫና የሚያስከትል ወጥነት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

4. **"ከመሬት በታች የሚካሄድ የቁፋሮ ሥራ"** ማለት ከመሬት በታች በመሳሪያና በእጅ ከሚደረግ የማዕድን ቁፋሮ እና ፍለጋ ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማለት ነው፡፡

5. **"ነፍሰ ጡር ሴት"** ማለት መጸነሷ በህክምና የተረጋገጠ ሴት ናት፡፡

6. **"ጨረራ"** ማለት ማንኛውም የውስጥ አካልና ህዋስን ሰንጥቆ የማለፍ ኃይል ያለው የኤሌክትሮ ማግኔትክ ሞገድ ነው፡፡

7. **"ለጤና ጐጂ የሆኑ ሥራዎች"** ማለት ከሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ወይም ከሥራ ሂደት የሚመነጩና በሴት ሠራተኞች ላይ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳት የማስከተል ውጤት ያላቸው ፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ስነ ሕይወታዊ፣ ኢርጉኖሚካልና ሳይኮሶሻል ጠንቆች ያሉባቸው ሥራዎች ወይም የሥራ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡

8. **"የመውለድ ሁኔታን የሚያውኩ ሥራዎች"** ማለት የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር የሚያስከትሉ እና የፅንስ ተፈጥሮአዊ ዕድገትን የሚያዛቡ ስለመሆናቸው በሳይንሳዊ ምርምር የተረጋገጠላቸው ካርሲኖጄኒክ

2. "Heavy Work" is work thatrequires the exertion of 7.0 kilo calories per minute of metabolic energy.

3. "Continuous Work" is uninterrupted and repetitious work that causes physical stress.

4. "Sub – terrane anExcavation Work" is work that is carried out underground by hand or machine and is related to mineral extraction and exploration.

5. "A Pregnant Woman" is one whose pregnancy has been certified medically.

6. "Radiation" is any electromagnetic wave that has the power to pass through internal organs and tissues.

7. "Works Harmful to Health" are those related to jobs or work processes that bring physical and psychological harm to women workers that may be caused by physical, chemical, biological, ergonomic, and psychosocial agents.

8. "Works that Adversely Affect Childbirth" are types of works in which carcinogenic, mutagenic, and teratogenic compounds of elements are utilize and its effect on reproductive problems, and that interfere with natural embryonic development is

ሙታጂኒክና ቴራቶጂኒክ ንጥረ ነገሮች ወይም የንጥረ ነገር ውህዶች አገልግሎት ላይ የሚውሉበት የሥራ ዘርፍ ነው፡፡

9. በአዋጅ አንቀጽ2 የተዘረዘሩት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

10. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 በሚሸፍናቸው አሠሪና ሴት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. ሴት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ ሥራዎች

1. ማንኛውም አሠሪ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ሥራዎች ላይ ሴት ሠራተኞችን ቀጥሮ ማሰራት የተከለከለ ነው፡-

   ሀ. በማዕድን ቁፋሮና ከመሬት በታች በሚካሄዱ ጥልቅ የጉድጓድ ወይም የዋሻ ቁፋሮ ሥራዎች፣

   ለ. ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ውህዶችን በመቀመም፣ በመበጥበጥ፣ በመሙላት፣ በማሸግ እና በመርጨት ሥራዎች፣

   ሐ. በእርሻ ማሳዎች ውስጥ ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ኬሚካሎችን በመርጨት ሥራ ማሰማራት የተከለከለ ነው፣

   መ. የአስቤስቶስና የአስቤስቶስ ውህድ ንጥረ ነገሮችን፣ በመፍጨት፣በመሞረድ እና በስራ ላይ እንዲውል በማድረግ

   ሠ. ጥልቅ ውሃ ወይም በቀላሉ ሊመረዝ

proven scientifically.

9. The definitions given in Article 2 of Labor ProclamationNo.1156/2011 shall be applicable

10. Provisions of this directive set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## 4. Scope of Application

This Directive shall be applicable to employers and women workers covered in Labor Proclamation No.1156/2011.

## 5. Works Prohibited for Women Workers

1. Employers are prohibited from employingwomen workers in the following jobs:

   a. Mineral extraction and in sub-terranean works like digging deep wells or excavating caves.

   b. Preparation of pesticides and herbicides, whetherit is in compounding, mixing, filling, packaging, or spraying them.

   c. Spraying of pesticides or herbicides in farm plots.

   d. Applying, filing, and poundingof asbestos and asbestos compounds.

   e. Working in a deep pool, or flowing water that can be easily poisoned.

የሚችል የፍሳሽ ውሃ ውስጥ ገብቶ መስራት

6. **<u>ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች</u>**

ማንኛውም አሰሪ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ሥራዎች ላይ ለተሰማሩ ሴት ሰራተኞች ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ ሊያደርግ ይገባል፡፡

1. በብረታ ብረት ማቅለጫ፣ በኤሌክትሮ ፕሌቲንግና መካኒካል ሥራዎች በባትሪ ፋብሪካዎች፣ ጨረር አመንጪ መሣሪያዎችን በሚጠቀሙ ድርጅቶች የተሰማሩ ሴት ሠራተኞች በሥራ ሂደት ለሚፈጠሩ አየር ወለድ ንጥረ ነገሮች እና የጨረር ሞገዶች የመጋለጥ ሁኔታ በአባሪ አንድ ከተዘረዘሩ የመጋለጫ ጣሪያ ደረጃዎች መብለጥ የለበትም፡፡
2. አሠሪዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩ የሥራ ዘርፎችና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለተሰማሩ ሴት ሠራተኞች ዓመታዊ የጤና ምርመራ ያደርጋሉ፡፡
   ሀ. ተስማሚ መቀመጫ በሌለበት ሁኔታ ለረዥም ሰዓታት በመቆም የሚሰሩ ሥራዎች፣
   ለ. በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ ከደምና ከሰውነት የውስጥ ፈሳሽ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች፣
   ሐ. የድንጋይ ወፍጮ /ካባ/ እና የድንጋይ ጠረባ ሥራዎች

6. **<u>Works that Requires Special Occupational Safety and Health Protection</u>**

Employer shall provide special occupational safety and health protection for women working jobs listed below:

1. Undertakings engaged in metal melting, electro- plating and mechanical works, battery factories, and in radiation-emitting instruments shall not expose women workers to air levels of pollutants and radiation waves above thelimitsgiven in Annex 1.

2. Employers shall provide annual health examinations for women engaged in the works and activities listed below:

   a. Those who work standing for a long time for lack of available appropriate seating arrangement.

   b. Those who work in health providing institutions and are in direct contact with blood and other bodily fluids.

   c. Those who work in stone quarries, and in stone carving.

መ. በመንገዶች ሥራ ውስጥ አስፋልት/ሬንጅ የማፍላትና የመርጨት ሥራ፣

ሠ. የመፀዳጃ ጉድጓዶችና የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦዎች የማፅዳት ሥራ፣

ረ. በሥራ ባህርያቸው ከፍተኛ ቅዝቃዜ /Cold/ እና ከፍተኛ ሙቀት /Hot/ ባላቸው የሥራ ዘርፎች፣

ሰ. የንዝረትና ሰውነትን የማንዘፍዘፍ (Vibration) ባህርይ ያላቸው ሥራዎች፡፡

## 7. <u>ለነፍሰ ጡር እና ለሚያጠቡ ሴት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 6 ከተጠቀሱ ሥራዎች በተጨማሪ በአባሪ ሁለት የተዘረዘሩ ለሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር መንስኤ ለሆኑ ንጥረ ነገሮችና የንጥረ ነገር ውህዶች በቀጥታ የሚያጋልጡ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴዎች ለነፍሰጡር ሠራተኞችና ከወሊድ በኋላ እስከ 6 ወራት ድረስ ለሚያጠቡ ሠራተኞች የተከለከሉ ናቸው፡፡

## 8. <u>ለሴት ሠራተኞች የተወሰነ የክብደት መጠን</u>

1. የሴት ሠራተኞችን ጉልበት በመጠቀም የሚካሄድ ማናቸውም ክብደትን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ ፣ የመሸከም ፣ የማጓጓዝ ፣ የማንሳት ፣ የማውረድ ፣ የማውጣት ፣ የመጎተት ፣ የመሳብና የመሳሰሉት ሥራዎች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን የክብደት መጠን ጣሪያ ሳያልፉ ይከናወናሉ፡፡

   ሀ. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ፡-

d. Those who work in heating asphalt and spraying it in road construction.

e. Those who work in cleaning toilets and drainage pipes.

f. Those whose nature of work exposes them to very cold or very hot temperatures.

g. Works that cause the body to shake or to limp.

## 7. <u>Works Prohibited for Pregnant and breastfeeding women</u>

Besides the works mentioned in Articles 5 and 6 above, those listed in Annex 2 that cause reproductive problems from direct exposure to elements and their compoundsare prohibited to pregnant workers and to nursing mothers for up to six months from the time of delivery.

## 8. <u>Weight Limit for Women Workers</u>

1. Women workers should not engage in moving, carrying, transporting, lifting, unloading, loading, dragging, or pulling goodsthat weigh above the following ceilings:

   a. Where the activity is wholly manual:

      i. For continuous work: 15

1. ተከታታይነት ላለው ሥራ እስከ 15 ኪ.ግ
2. ተከታታይነት የሌለው ሥራ እስከ 25 ኪ.ግ

ለ. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ ዳገት የመውጣትና ቁልቁለት የመውረድ ሁኔታ ባለበት፡-

1. ሥራው ተከታታይነት ካለው የዕቃው ክብደት እስከ 10 ኪ.ግ.
2. ሥራው ተከታታይነት ከሌለው የዕቃው ክብደት እስከ 15 ኪ.ግ.

ሐ. እንቅስቃሴው ባለ አንድ እግር ጋሪ በመጠቀም ከሆነ የዕቃው ክብደት እስከ 50 ኪ.ግ.

kgs.

ii. For non – continuous work: 25kgs.

b. Where the activity is wholly manual, but involves climbing up and downa slope:

i. For continuous work:10kgs.

ii. For non – continuous work: 15 kgs.

c. If the activity is carried out on a one-wheel barrow, the weight of the material can be up to 50kgs.

## 9. ስለ ኃላፊነት

ማንኛውም አሠሪ የሚከተሉት ሀላፊነቶች መፈፀም ይኖርበታል፡-

1. ሴት ሠራተኞች ወይም ነፍሰ ጡር ሠራተኞች ወይም የሚያጠቡ ሠራተኞች የሚሰሩት ሥራ ክልከላ የተደረገበት ሆኖ ከተገኘ የሥራ ደረጃቸውንና ደመወዛቸውን ሳይቀንስ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራትና በጠንቆቹ ምክንያት የጤና ጉዳት ያለመከሰቱን ማረጋገጥ፤

2. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱና ክልከላ የተደረገባቸው ወይም ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን የሥራ እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ ሴት ሠራተኞች

## 9. Responsibility

An employer has the following responsibilities:

1. when found women workers, pregnant workers or breastfeeding workers engaged in prohibited work, the employer shall transfer the worker to another job without a reduction in wage, or demotion in job position, and ensure that they have not suffered from any harm to their health.

2. An employer should provide awareness training and information on appropriate precautionsshall be taken by women workersregarding

ሊያደርጉት ስለሚገባ ጥንቃቄ መረጃና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፤

3. የመመሪያውን አተገባበር በተመለከተ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን የሚሰጡ ትዕዛዞችን ተፈፃሚ ማድረግ፤

4. ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን በግማሽ ዓመት አንድ ጊዜ የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 10. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የሚመለከተው አካል ወይም ግለሰብ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 11. ስለ ቅጣት

ማንኛውም አሠሪ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ድንጋጌዎችን ቢጥስ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስለ ቅጣት የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል፡፡

## 12. መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በየወቅቱ እየገመገመ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 13. የተሻረ መመሪያ

ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤናቸው የመውለድን ሁኔታ ስለሚያውኩ ጎጂ የሆኑ ሥራዎችን ለመወሰን ሚያዝያ 2005 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ተሽሯል፡

prohibited work, professional and health safety that have been incorporated in this Directive.

3. An employer should implement orders related to the Directive that are given by the Ministry or appropriate authority.
4. An employer should submit an implementation report to the Ministry or appropriate authority every six months.

## 10. Obligation to Cooperate

Any stakeholder, corporate or individual, has the duty to cooperate in the implementation of this Directive.

## 11. Penalty

Any employer that contravenes the regulations listed in this Directive shall be subject to the penalties decreed in Labor Proclamation No.1156/2011.

## 12. Modification of the Directive

The Ministry may periodically assess the implementation of this Directive and modify it.

## 13. Repealed Directive

The Directive issued in April 2005 on types of works which are particularly hazardous or dangerous to the health and to the reproductive systems of women is here by repealed.

## 14. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትር ከተፈረመበት ከነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)
የሠራኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

## 14. Effective date of the Directive

This Directive shall be in effect from the date of signing by the Minster on 18 August 2021.

Addis Ababa
ErgogieTesfaye (PhD)
Minister of
The Ministry of Labour and Social Affairs

## አባሪ 1፡ ልዩ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ኬሚካሎች

| | |
|---|---|
| **ሀ. ሜሪኩሪ** | **0.05 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ለ. ዚንክ** | **1.0 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ሐ. ማንጋኒዝ** | **5.0 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **መ. ካትሚ□ም** | **0.1 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ሰ. ሊት / □ርሳስ/** | **0.15 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ረ. አርሳይን** | **0.20 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ሠ. ካርቦን ብላክ** | **3.5 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ቀ. የብረት ኦ□ሣ□ት □□ም** | **10.0 ሚ/□ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **በ. ኮፐር/ መቴበ/ □□ም** | **0.1 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ተ. ፎስፋይን** | **0.4 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ቸ. ናይትሪክ ኦክሳይድ** | **30 ሚ/ግ በሜትር ኪዩብ አየር** |
| **ኘ. የጨረር ሞገድ / አዮናይዚንግ/** | **3 - 5 ዶዝ ኮንሰንትሬት** |

## አባሪ 2፡ ለነፍሰ ጡር እና ለሚያጠቡ ሴት ሠራተኞች የተከለከሉና ለሥነ ተዋልዶ ጤና ችግር መንስኤ የሆኑ ንጥረ ነገሮችና የንጥረ ነገር □ህዶች

- **አስቤስቶስ /Asbestos/**
- **አክሪሎናይትራይል /Acrylonitrile /**
- **አንቲሞኒ / Antimony /**
- **አዮናይዚንግ ሪዲዬሽን / Ionizing radiation /**
- **አርሴኒክ / Arsenic /**
- **ቦሪክ አሲድ / Boric Acid /**
- **ቤንዚን / Benzene /**
- **በሪሊ□ም / Berylium /**
- **ካትሚ□ም / Cadmium /**
- **ካርቦን ሞኖክሳይድ / Carbon monoxide /**
- **ካርቦን ዳይሰልፋ□ት / Carbon disulfide /**
- **ካርቦን ቴትራክሎራይድ / Carbon tetra chloride /**
- **ክሎሪኒትድ ሃይድሮካርቦንስ / Chlorinated Hydrocarbons /**
- **ክሎሮቤንዚን / Chlorobenzene /**
- **ኮባልት /Cobalt/**
- **□ሎሮ□ርም/Chloroform/**
- **□ሮሚ□ም እና የክሮሚየም ውሁዶች /Chromium & Chromium Compounds/**
- **ቴ□ሜታይል ፎርምአልዲሃይድ /Dimethyl Formaldehyde/**
- **ኢፒክለሮ ሃይድሪን /Epichlorohydrin/**
- **ኢታይሊን ዳይአሚን ቴትራአሲቲክ አሲድ/Ethylene diaminetetraacetic/**
- **ኢታይሊን ዳይብሮማይድ /ዳይክለራይድ/Ethylene dibromidedichloride /**
- **ኢታይሊን አክሳይድ /Ethylene Oxide/**

- **ክሎሮፍሎሮሜቴን /ፍሪዮን/ /Chlorofloromethane/**
- **ሊት እና ሊድ አክሳይድ Lead & Lead Oxide**
- **ኒኬል / Nickel/**
- **ናይትረስ ኦክሳይድ / Nitrous Oxide /**
- **ማንጋኒዝ / Manganese /**
- **ሊቲ□ም / Lithium/**
- **ሜርኩሪ /Mercury /**
- **ሜታይል ኢታይል ኪቶን /Methyl ethy ketone/**
- **ሞሊቢቴነም ትራይኦክሳይድ /Molybdenum trioxide/**
- **ናይትሪክ ኦክሳይድ / Nitric Oxide/**
- **ፐርክሎሮኢታይሊን /Perchloro ethylene/**
- **ፊኖል /Phenol/**
- **□ስ□ረስ / Phosphorus /**
- **ፓሊክሎሪኔትድ ባይፔኒልስ /Polychlorinated biphenyls/**
- **ቶሉን /Tolune/**
- **ትራይክሎሮኢታይሊን /Trichloro ethylene/**
- **ቲታንየም ዳይኦክሳይድ /Titanium dioxide /**
- **ቪኒል ክሎራይድ /Vinyl chloride/**
- **ዛይሊን /Xylene/**
- **ዚንክ ክሎራይድ /Zinc chloride /**